ስለዚህም በተደጋጋሚ ለባለሥልጣናት ባሃኦላህን ከሰሱ። በመጨረሻም የፋርስ መንግሥት ከአንዳንድ የኦቶማን ግዛት ባለሥልጣናት ጋር በማበር ከትውልድ ሃገሩ ይበልጥ እንዲርቅ ቁስጥንጥንያ ወደተባለች ከተማ አጋዙት።

ለባግዳድ ሕዝብ እ.ኤ.አ ኤፕሪል 1863 የትልቅ ሐዘን ወር ነበር። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያፈቀሩት የመጡት ወዳጃቸው ከተማቸውን ለቅቆ ወደማያውቁት ቦታ ሊሄድ ሆነ። ከተማዋን ከመልቀቁ ጥቂት ቀናት በፊት ከባግደድ ወጣ ብሎ በምትገኝ መናፈሻ ድንኳን አስጥሎ ሊሰናበቱት የመጡትን ብዛት ያላቸው ሰዎች ለአስራ ሁለት ቀናት አስተናገደ። የባብ ተከታዮች ወደዚያ መናፈሻ የሚሄዱት በከፍተኛ ሐዘን ነበር። ከባብ ተከታዮች ጥቂቶቹ አብረውት እንዲጋዙ ተወሰነ፤ አብዛኛዎቹ ግን እዛው እንዲቀሩ ስለተደረገ በከፍተኛ ሃዘን ተውጠው ነበር። ይሁንና ይህ ጊዜ የሐዘን እንዲሆን አምላክ አልፈቀደም። የበረከቱ በር በሰፊው ተከፈተ። ባሃኦላህም ባብ "እርሱ እግዚአብሔር የሚከስተው" እያለ የተነበየለት እርሱ እንደሆነ በዙሪያው ለነበሩት አወጀ። ሐዘን ወሰን በሌለው ደስታ ተተካ። ልቦች ተነቃቁ ነፍሶችም በእርሱ ፍቅር እሳት ተለኮሱ። እነዚያ ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ ሜይ 2 ያሉት አስራ ሁለት ቀናት በመላው የባሃኢ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚከበሩ በዓላት እንዲሆኑ ባሃኦላህ ደነገገ።


ቁስጥንጥንያ የኦቶማን ቱርክ ግዛት ዋና ከተማ ነበረች። የባሃኦላህ ጥበብና ግርማ እዚያም ቢሆን ብዙ ሰዎችን መሳብ ጀመረ። በቁስጥንጥንያ መቆየት የለበትም ሲሉ አክራሪዎቹ የእስልምና ቀሳውስት አጉረመረሙ። ባለስልጣናቱን ካሳመኑ በኋላ አድርያኖጵሎስ ወደ ምትባል ከተማ እንደገና አጋዙት። በአድርያኖጵሎስም ባሃኦላህ የጭቆና አሰራራቸውን ትተው ለሕዝቦቻቸው እድገት እራሳቸውን እንዲሰጡ ጥሪ በማድረግ ለዓለም ነገሥታትና የሃይማኖት መሪዎች ጽላቶችን ገለጸ።

ከዚህ በኋላም ጠላቶቹ እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላው ቅጣት አውጠነጠኑ። በዚያን ጊዜ በኦቶማን ግዛት ውስጥ ካሉት ሁሉ እጅግ አስከፊ ወደነበረው፣ በእስራኤል አገር በሚገኘው የአቆር የእስር ከተማ ከነቤተሰቡ እናግዘው ሲሉ አሰቡ። የእስር ከተማውን አስከፊ ሁኔታ መቋቋም ስለማይችል እዚያው ይሞታል በማለት አስበውም ነበር። አምላክ እራሱ የለኮሰውን ምንም ሊያጠፉ እንደማይችል እነዚህ ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አላጤኑም ነበር። ባሃኦላህ በአቆር የደረሰበት ችግር ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ለመግለጽ ያዳግታል። በመጀመሪያ በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ብቻውን ታሰረ። ልጆቹ እንኳን እንዲያዩት አልተፈቀደላቸውም ነበር። ምንም ዓይነት መፈናፈኛ ሳያገኝ ቀንና ሌሊት በጠላቶቹ ተከበበ። ይሁንና የእስሩ ሁኔታ ቀሰ በቀስ እየተለወጠ መጣ። የአቆር ነዋሪዎችና መንግሥት ወደ ከተማቸው የተጋዙት ጥቂት ባሃኢዎች ወንጀል የሌለባቸው መሆናቸውን እያመኑበት ሄዱ። ምንም እንኳ አብዛኛው ሕዝብ የባሃኦላህን ትልቅ ደረጃ ባያውቁም አሁንም ብዙ ሰዎች በእርሱ ጥበብና ፍቅር መሳብ ጀመሩ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የእስር ከተማው በሮች ለባሃኦላህና ለተከታዮቹ ክፍት ሆኑ። በመጨረሻም የተሻለ ምቾት ባለው ባሕጂ በሚባል ቤት እንዲኖር ተፈቀደለት። በዚያም በከፍተኛ ክብርና ግርማ እየኖረ ሳለ እ.ኤ.አ ሜይ 1892 ከዚህ ዓለም ተለየ።

ባሃኦላህ የዓለም አቀፍ ሰላምና ወንድማማችነትን ሰንደቅ ተክሏል። የእግዚአብሔርን ቃል ከስቷል። ምንም እንኳን ጠላቶቹ ኃይላቸውን አስተባብረው ቢነሱበትም በቴህራን በሰንሰለት ታስሮ በነበረበት ወቅት አምላክ ቃል እንደገባለት በጠላቶቹ ላይ ድልን አግኝቷል። በሕይወት ዘመኑ የእርሱ መልዕክት የብዙ ሺህ ሰዎችን ልቦች ያነቃቃ ሲሆን ብዙዎችም በእርሱ መንገድ ሕይወታቸውን ሰጥተዋል። ዛሬም የእርሱ ትምህርት በዓለም ዙሪያ መሰራጨቱን እንደቀጠለ ነው። የሰውን ዘር በአንድ ዓለም አቀፍ ሃይማኖት አንድ ለማድረግ ያቀደውን የመጨረሻ ግቡን ሳይቀዳጅ ምንም ሊቋቋመው አይችልም።


ለበለጠ ማብራሪያ
ባሃኢ ማዕከል
ስልክ፡ 0116627751
ፖ.ሣ.ቁ.102 ፥ አዲስ አበባ
ኢ.ሜል፡bahais.eth@ethionet.et


# የባሃኦላህ ሕይወት



# ባሃኦላህ

እ.ኤ.አ ኖቬምበር 12 ቀን 1817 የፋርስ (ኢራን) ዋና ከተማ በሆነችው በቴህራን ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ የታላቅነት ምልክቶች ይታዩበት ነበር። በዚህ ባህሪው ምክንያት ትልቅ ደረጃ እንደሚጠብቀው ወላጆቹ አመኑ። በንጉሡ ዘንድ ልዩ የሚንስትርነት ማዕረግ ያላቸው አባቱ ልጃቸውን በጣም ይወዱት ነበር። አንድ ቀን በሕልማቸው ባሃኦላህ በጣም ሰፊ ከሆነ ባህር ውስጥ ሲዋኝ ያዩታል። ከሰውነቱ የሚፈልቀው ብርሃን ሰፊውን ባህር እንዲያበራና እንዲያንፀባርቅ አድርጎታል። ጥቁር ፀጉሩ በሁሉም አቅጣጫ ተንሳፎ ያብረቀርቅ ነበር። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ዓሳዎች በዙሪያው ተሰብስበዋል። እያንዳንዱም ዓሳ አንዱን የፀጉሩን ቅንጣት ይዟል። ጸጉሩን የያዙት ዓሳዎች ብዙ ቢሆኑም አንዲት የፀጉር ቅንጣት እንኳን አልተነቀለችም። በነፃነትና ያለምንም ገደብ በውሃው ላይ ሲንሳፈፍ ሁሉም ይከተሉት ነበር። የባሃኦላህ አባትም በሕልም ፈቺነቱ የታወቀን ጠቢብ የህልሙን ፍቺ ጠየቁት፣ ሰውየውም ወሰን የሌለው ባህር መላው የሰው ዘር እንደሆነና ልጃቸውም ለብቻውና ያለምንም ረዳት በሰው ዘር ላይ ንግሥናን እንደሚቀዳጅ ነገራቸው። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ዓሳዎችም በዓለም ህዝቦች መካከል የሚያስነሳውን ንቅናቄ ይወክላሉ። ነገር ግን የኃያሉ አምላክ የማያቋርጥ ጥበቃ ሰለሚከተለው ማንም ሊጎዳው አይችልም በማለት ሕልሙን ፈታላቸው።

ባሃኦላህ ገና በ14 ዓመቱ በጥበቡና በእውነተኛነቱ በንጉሡ እልፍኝ የታወቀ ነበር። አባቱ በሞቱ ጊዜ የእርሳቸውን ከፍተኛ ቦታ እንዲተካ ከንጉሡ ጥያቄ ሲቀርብለት 22 ዓመቱ ነበር።

ባሃኦላህ ግን አለማዊ ጉዳዮችን ለማስተዳደር የሚያውለው ጊዜ አልነበረውም። የንጉሱን እልፍኝና ሚኒስትሮቹን ወደ ኋላ ትቶ በኃያሉ አምላክ የተመደበለትን ጎደና መከተል ቀጠለ። ጊዜውን ጭቁኖችን፣ ህሙማንና ድሆችን በመርዳት ያሳልፍ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ባሃኦላህ የድሆች አባት በሚባል ስም ይታወቅ ጀመር።

በሃያ ሰባት ዓመቱ ከአንድ ልዩ መልዕክተኛ የባብን ፅሑፎች ተቀበለ። ባብ አዲስ የእግዚአብሔር ክስተት የሚገለጽ መሆኑንና ለዓለም ሰላም ፣ አንድነትና ፍትህ የሚመጣበት ፣ ለረዥም ዘመናት ሲጠበቅ የቆየው የአምላክ ቀን መድረሱን ያወጀ የአምላክ ክስተት ነው። ወዲያውኑ ባሃኦላህ የባብን መልዕክት ተቀበለ፤ ከጠንካራ ተከታዩቹም አንዱ ሆነ። የፋርስ (ኢራን) ሕዝብ መሪዎች በእኔነት ስሜቶቻቸው ታውረው የባብን ተከታዮች በአሰቃቂ ጭካኔ ማሰቃየት ጀመሩ። ምንም እንኳን ባሃኦላህ ከተከበረ ቤተሰብ የተወለደ መሆኑ ቢታወቅም የዚህ ጭካኔ ተጠቂ ሆነ።

ባብ ማንነቱን ካወጀ ከስድስት ዓመታት በኂላ በ31 ዓመቱ በመንግሥት ትዕዛዝ አደባባይ ላይ ተሰቅሎ በ750 ወታደሮች ተኩስ ሰማዕትነትን ተቀበለ።
ባሃኦላህም ጥቁር ጉድጓድ በተባለ ከምድር በታች በሚገኝ እስር ቤት ውስጥ ተጣለ። በአንገቱ ዙሪያ አሸክመውት የነበረው የብረት ሰንሰለት በጣም ከባድ ስለነበር ጭንቅላቱን ቀና ማድረግ እንኳን አይችልም ነበር። በዚያም እስር ቤት በኃይለኛ ስቃይ የተሞሉ ወራትን አሳለፈ። ይሁንና ነፍሱ በአምላክ መንፈስ የተሞላውና ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው ታላቁ የእግዚአብሔር ክስተት እንደሆነ የተገለጸለት በዚህ እስር ቤት ሳለ ነበር። ከዚህ ጨለማ ወህኒ ቤት የባሃኦላህ ፀሐይ ፈንጥቃ በፍጥረት ሁሉ ላይ አንፀባረቀች።

በጥቁር ጉድጓድ እስር ቤት አራት ወራት ካሳለፈ በኃላ ንብረቱን ሁሉ ተዘርፎ ከነቤተሰቡ ለስደት ተዳረገ። በጣም ቀዝቃዛ በሆነው የክረምት ወራት በምዕራባዊው የፋርስ ተራራ በኩል በዚያን ጊዜ የኦቶማን ግዛት ወደ ነበረችው የአሁን ኢራቅ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ባግዳድ ተጋዙ። ወደ ባግዳድ ከተማ ለመድረስ በበረዶ የተሸፈነውን የፋርስ ተራሮችን ለማቋረጥ ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮችን ሲጓዙ የደረሰባቸውን መከራ ቃላት ሊገልጹት አይችልም።

ብዙም ሳይቆይ የባሃኦላህ ዝና በባግዳድና በአካባቢው ባሉ ሌሎች ከተሞች በመሰራጨቱ የተጋዘውን እስረኛ ቡራኬ ለመቀበል ወደ እስር ቤት የሚመጡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ። ባሃኦላህ በጣም ታዋቂ በመሆኑ ቅናት ያደረባቸውም ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ መካከል በባሃኦላህ ፍቅራዊ ጥበቃ ሥር ይኖር የነበረው ወንድሙ ሚርዛ ያሕያ ነበር።
በጊዜው የባብ ተከታዮች ለሚርዛ ያሕያ ትልቅ ከበሬታ ያሳዩት ስለነበር ባሃኦላህን የተቃወመው የባብ ተከታዩች መሪያቸው ያደርጉኛል ብሎ በማሰብ ነበር። የእግዚአብሔር ክስተት በተገለጸ ጊዜ ለእርሱ ታዛዥ በመሆን የሚኖሩ እውነተኛ ታላቅነትን ይቀዳጃሉ። የቅርብ ዘመዶቹ ቢሆኑም እንኳን እርሱ ከሌሎች ሰዎች የተለየና ማንም የማይጋራው ደረጃ እንዳለው መርሳት የለባቸውም።

የሚርዛ ያሕያ ሴራ በተከታዩቹ ዘንድ መከፋፈልን በማምጣቱ ባሃኦላህ በጣም አዘነ። አንድ ሌሊትም ለማንም ሳይናገር ቤቱን ትቶ በኢራቅ ወደሚገኘው ወደ ኩርዲስታን ተራሮች ሄደ። በዚያም ከማንም ሳይገናኝ የፀሎትና የሱባኤ ሕይወት አሳለፈ። ማንም ከየት እንደመጣና ማን ተብሎ እንደሚጠራ አያውቅም ነበር። ይሁንና ቀስ በቀስ የአካባቢው ሰዎች በአምላክ የተቸረ እውቀት ስላለው አንድ ታላቅና ስም የለሽ ጻድቅ ሰው ማውራት ጀመሩ። የዚህ ቅዱስ ሰው ዜና የባሃኦላህ ትልቅ ልጅ ወደሆነው አብዱል ባሃ ዘንድ ሲደርስ ይህ ቅዱስ ሰው ተወዳጁ አባቱ እንደሆነ ወዲያውኑ አወቀ። ከልዩ መልዕክተኞችም ጋር ወደ ባግዳድ እንዲመለስ ባሃኦላህን የሚለምኑ ደብዳቤዎች ተላኩ። ይህንን ልመና በመቀበሉ ለሁለት ዓመታት የቆየው አሳዛኝ መለያየት አበቃ።

ባሃኦላህ ተገልሎ በቆየባቸው ጊዜያት የባቢ ኅብረተሰብ ሁኔታ በፍጥነት አሽቆልቁሎ ነበር። ባሃኦላህም የተሰቃዩትንና ግራ የተጋቡትን የባብ ተከታዩች በአዲስ መንፈስ መሙላት ጀመረ። ምንም እንኳን የዘመኑ የእግዚአብሔር ክስተት እንደሆነ ያላወጀ ቢሆንም የቃላቱ ኃይልና ጥበብ ብዛት ያላቸው ባቢዎችን የጽኑነት ኃይል ከማስታጠቁ በተጨማሪ በተለያዩ የሕይወት ጎዳና ላይ የተሰማሩ ሰዎችን አድናቆት አተረፈ። ይሁንና አክራሪ የእስልምና ቀሳውስትና ቀናተኛ ወንድሙ ሚርዛ ያሕያ እንደዚያ ብዛት ባላቸው ነፍሶች ላይ የሚያደርሰውን የመለወጥ ውጤት በዝምታ መመልከት አልቻሉም።